# የኢትዮጵያ ዝምታ

ከአይምሮ ዳኛቸው

በቅርቡ ተስፋዬ ገ/አብ የተባለ በትውልዱ ኤርትራዊ የሆነ የወያኔ ጋዜጠኛ አንድ መጽሐፍ የሚመስል ቁርጥራጭ ወረቀቶችን ጫጭሮ ሰሞኑን በትኗል ። ይሄንን መጽሐፍ በተመለከተም በየድረ ገጹ እጹብ ድንቅ እየተባለና እየተወደሰ ሲነገር አይቼ ተገርሜያለሁ ፤ ይሄው  የወያኔ  ጋዜጠኛ ነኝ ባይ ከዚህ ቀደም "የቡርቃ ዝምታ" በሚል ርዕስ ሕዝብ በሕዝብ ላይ እንዲነሳሳ ለማድረግ  የደም መፋሰስን ለማየት ካለው ክፉ ምኞት የተነሳ የሌለ ታሪክ ሲያቦካና ሲለቀልቅ አንተ ማነህ ከየትስ መጣህ  ብሎ የጠየቀው ባለመኖሩና ላቀረበውም ተራ ፍሬፈርስኪ አስፈላጊውን መልስ ስላልተሰጠው  ዛሬም በድጋሚ  የልብ ልብ ተሰምቶት በተለመደው ጎልዳፋ ብዕሩ የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሬ ወንድሞቹ ላይ እንዲነሳ ለማድረግ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" በሚል ቁርጥራጭ ወረቀቶች  ሰባስቦ በየቦታው አሰራጭቷል ። ይህንንም መጽሐፍ አነበብን የሚሉ ግለሰቦችም ምኑን አይተውና ተገንዝበው እንደሆነ አድናቆታቸውን የሚያሳዩት ለኔ ግልጽ አልሆነልኝም ። ምኑ ላይ እንደሆነ የዚህ ስንክሳር  ድንቅነቱ ሊገባኝ አልቻለም ፤ ጸሐፊውን ለማድነቅ የተሯሯጡት ግለሰቦች ጸሐፊው  ስለምን እንደሚያወራ አልገባቸውም አሊያም የሱን ሀሳብ የሚጋሩ የኢትዮጵያን ውድቀት የሚመኙ ቅጥረኞችና ግንጠላን ደጋፊዎች  ከመሆን አያልፉም ።

ተስፋዬ ለኢትዮጵያ መጥፋትና መፈራረስ ዘዴ አድርጎ የወሰደው  ልቡ ውስጥ አምቆት የቆየውን እኩይ ሀሳብ ተግባራዊ ለማድረግ ፤ የአገራችንን አንድነቷን ለማናጋት ፤ ሕዝብና ሕዝብን ለማጋጨት ይበጃል ብሎ ያሰበውን መሰሪ ስራውን እንደፈጣሪዎቹ ኢሳያስ አፈወርቂና መለስ ዜናዊ እሱም የአቅሙን ለመወጣት ሲደክምና ሲፍጨረጨር ተስተውሏል ። በገበያ ላይ የበተናቸው ሁለቱም መጽሐፎች በጥላቻና በበቀል ተጸንሰው ፤ በጥላቻና በበቀል የተወለዱ ፤ ሲሆኑ እንኳን ለመነበብ ለኪዮስክ ስኳር መጠቅለያነትም መብቃት የማይገባቸው በርካሽ ግለሰብ ፤ በርካሽ ቀለም ፤ በርካሽ ወረቀት ላይ የተሞነጨሩ የጥላቻ ዶሴዎች በመሆናቸው ፤ ቢቻል የተገኘውን መጽሐፍ ሁሉ ሰብስቦ ከማቃጠል በቀር አንባቢያን እንዲጎበኟቸው አልጋብዝም ።

ይህ ግለሰብ የንዋይ ወይም የቁሳዊ ንብረት ደሃ ሳይሆን ነገር ግን የአይምሮ ድህነት ክፉኛ የተጫነው ግለሰብ እንደሆነ ከጽሁፉ ለመረዳት ይቻላል ፤ የበታችነት የነገሰበትና እራሱን እንዲጠላ ሆኖ የተፈጠረ እንደሆነ በራሱ ላይ መስክሯል ። ይህንን ለዘመናት የሚያሰቃየውን የትንሽነት በሽታ በተቻለ ራሱ ችሎ እንደማስታመም ደዌውን ወደ ሕብረተሰብ ለማዝመት ያልተቆጠበ ጥረት የሚያደርግ የዲያቢሎስ የበክር ልጅ ነው ማለቱ ግለሰቡን ባጭሩ ጥሩ አድርጎ ይገልጸዋል ብዬ አምናለሁ።

ግለሰቡ ማንነቱን ሲገልጽ ቤተሰቦቹ ከኤርትራ ፈልሰው ደብረዘይት የሰፈሩና እሱም እዚያው ደብረዘይት ተወልዶ ያደገ ፤ ብሎም እዚያው አካባቢ የተማረ መሆኑን ይገልጻል ፤ ታዲያ እሱና ቤተሰቦቹ ትላንትና ከሰሜን ፈልሰው ደብረዘይት እንደሰፈሩ እየነገረን ፤ እራሱን እንደ አካባቢው ሕዝብ ሲመለከትና ለአካባቢው ሕዝብ ተቆርቋሪና አዛኝ አድርጎ ሲያቀርብ ፤ እሱም ሆነ ወላጆቹ ፤ ወይንም ምንጅላቶቹ ከመወለዳቸው በፊት በቦታው የነበሩትን ፤ እርስ በርስ ተጋብተውና ተዋልደው የሚኖሩትን እንደ ትላንትና መጤዎች አድርጎ ሲናገር ትንሽ አፋ ላይ መራራ ስሜት እንኳን  የማይሰማው አይኑን በጨው የታጠበ ፤ “በኋላ የመጣ አይን አውጣ” እንደሚሉት የሆነ የስራዬ ቤት ጋዜጠኛ እንጂ ፤ ጋዜጠኝነት ሙያ ባለፈበትም አልፎ የማያውቅ  መሆኑን በግልጽ አሳይቶናል  ።

ተስፋዬ አንደበቱ ያልተገራ ፤ እራሱ ተዋርዶ ሌላውን ለማዋረድ ወደኋላ የማይል ፤ ግለሰብ እንደሆነ እምዬ ሚኒልክን ከፍ ዝቅ እያደረገ በመሳደብና በማዋረድ አስመስክሯል ። ምኒሊክን በፈጠራ ሲወነጅል ፤ ህሊናው ያልሞገተው ፤  ያልጸጸተው ፤ ለከት የሌለው ሽርክት አፍ ብቻ ሳይሆን ፤ በመረቱ የጎዳና ቃላቶች አፉን የሚያለቀልቅ እንደሆነ ለመገንዘብ አስችሎናል ። መቼም ትንሽ ሰው አንሶ ያሳንሳል እንዲሉ ፤ ሚኒልክን አንተ እያለ ሲጠራ ምንኛ አሳዳጊ የበደለው ፤ ጋጠወጥ ፤ የጎዶሎ ቀን መራራ ፍሬ እንደሆነ ነግሮናል ፡፡

ይህንን ስም አይጠሬ ቀፍቅፈው ያሳደጉት ወሮበሎች ፤ ኢሳያስና መለስ እንኳን ፤ ምንም ሁለቱም ግለሰቦች የኢትዮጵያ ምድር ያበቀለቻቸው ጭራቆች ቢሆኑም ቅሉ ፤ እነሱ ለተቀመጡበት ወንበር ክብር

ሲባል እንኳን አንቱ ተብለው ይጠቀሳሉ ፤ አይደለም እምዬ ሚኒሊክ ፤ አጼ ሚኒሊክ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ክብር ብቻ ሳይሆኑ፤ የመላው አፍሪካ መኩሪያ እንደሆኑ እኛ የምንለውን ሳይሆን ፤ እንደ ፈጣሪ የሚያምናቸውን ፈረንጆች ስለ ምኒሊክ ማንነትና ምንነት የጻፉትን መጽሐፍ አገላብጦ መረዳት በቻለ ነበር ። ጋዜጠኛ ማለት አንዱ ትልቁ የሙያ ተግባሩ በርካታ መጽሐፍትን ፤ መዛግብትን ፤ ማገላበጥና ማገናዘብ ፤ መመርመር ተቀዳሚ ተግባሩ መሆን የነበረበት ፤ ያልታደለው ጋዜጠኛ ነኝ ባይ ግን አሉባልታ ሲወቅጥና ሲያመነዥግ ፤ እድሜውን ባድርባይነት ሲገፉ የኖረ ፤ ወደፊትም በዚሁ ሁኔታ ሕዝብን እያሳዘነ ለመኖር የቆረጠ ለመሆኑ አያጠራጥርም ።

ይህ አይነኬ ቀድሞ ከወያኔ ጋር በነበረበት ወቅት ይሰራ የነበረውን ግፍ ደብቆ የሌሎች ጓደኞቹን ወንጀል አጉልቶ ስለተናገረ ብቻ ፤ እራሱን ከደሙ ንጹህ አድርጎ ለማስቀመጥ ይሞክራል ፤ በኑዛዜውም ምንም የማናውቀው ሚስጥር አልነገረንም ፤ ሊነግረንም አይችልም ፤ ጽሁፉን አጥብቆ ለመረመረው በእውነት ምን አዲስና የማናውቀው ነገር ሰለ ወያኔዎች የነገረን ነገር አለ? ብለን እራሳችንን ብንጠይቅ መልሱ ምንም ሆኖ እናገኘዋለን ። ወያኔ ተስፋዬ ከነገረን አስር እጅ የከፋ ተግባሮችን የፈጸመ ፤ እየፈጸመም ያለ ለመሆኑ የሱ ምስክርነት አያሻንም ።

ስለ ወያኔ ጸባይም ሆነ የአሰራር ዘይቤ ፤ ወያኔ የሚቃወማቸውን እንዴት እንደሚያጠፉ ፤ አገርና ሕዝብ እንዴት እንደሚከፋፍሉ ፤ የራሳቸው የሆነን መሃይም ካድሬ እንዴት አድርገው ወደ ስልጣን እንደሚያመጡ ፤ ንብረት እንዴት እንደሚዘርፉ ፤ ሌሎች ሌሎችም ብንመለከት ይህ ትላንት አብሮ ሲገድልና ሲያስር የነበረ ፤ የስርአቱ ዋልታና ምሰሶ ፤ ዛሬ በአስራአንደኛው ሰዓት ላይ መጥቶ ስለ ወያኔ ቀድሞ የማናውቀው ምንም አዲስ ነገር ሊነግረን አይችልም ። እሱ ኑዛዜዬ ብሎ ያስቀመጣቸው ውስጥ ወቸ ጉድ! እንዲህ ያደርጋሉ እንዴ? ብሎ ያስደነቀን ምን አዲስ ነገር አለ? ምናልባት የየግለሰቦችን የስራ ድርሻቸውን እኛ ከምናውቀው በተሻለ ቤተኛ ስለነበረ ከማብራራቱ በቀር ምን ተአምር የሚያሰኝ ሚስጥር ነግሮን ነው? ተስፋዬ ከወያኔ ጋር በሚበላበትና በሚጠጣበት ወቅት ወያኔዎችን ለማስደሰት ብሎ የኦሮሞ ሕዝብ በአማራው ወገኑ ላይ እንዲነሳ ጥላቻን የሚያስፋፋ ልብ ወለድ የፈጠራ ታሪክ በማቀነባበር መሰሪ ዘመቻውን በአማራው ላይ ሲያራምድ ከቆየ በኋላ አሁን ደግሞ ወያኔዎች የሻቢያ ቅጥረኛ ነው ብለው ከማህበራቸው ሲያስወግዱት ቁጭቱን በወያኔ ላይ የተወጣ አስመስሎ የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሬ ወንድሞቹና እህቶቹ ላይ እንዲዘምት የሚገፋፋ እኩይ መልእክቱን ይዞልን ብቅ አለ ። ለምን አብሮ ከወያኔ ጋር በሚሰራበት ወቅት ይህንን ሁኔታ አላሳወቀንም ነበር? ጊዜ አጥቶ? አዎ የሰው ደም ሲያፈስ ምን ጊዜ ነበረው ። በየጊዜው ተስፋዬን የመሳሰሉ ከወያኔ ፍርፋሪ ሲለቃቀሙ ሕዝብና አገር ሲበድሉ ቆይተው የፍርፋሪው ቧምቧ ሲቋረጥባቸው ከመቼው ተገልብጠው የወያኔ ጸረ ሕዝብነት እንደሚታያቸው ሳስበው ይገርመኛል ፤ መቼም በሆዱ የሚያስብ የሆዱ መደጎሞያ ሲቋረጥ ነው ከእንቅልፌ ነቃሁ በማለት የሕዝብ ወገን ለመምሰል ያለ የሌለ መቀባጠር የሚጀምረው ፤ ግሩም ነው የኛ የድል አጥቢያ አርበኞች ፤ ትገርማላችሁ ከማለት በቀር ምን ይባላል?

እንግዲህ የዚህ ግለሰብ የአይምሮ ብስለትና ብልጥነት ከራሱ ጥቅም ጋር በተያያዘ ፤ በራሱ ዙሪያ የሚሽከረከር ብቻ እንደሆነ ያመለክተናል ፤ "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" እንዳለችው አህያ ማለት ነው ።

እዚህ ላይ ግን አንድ በጣም ተመሳሳይ የሆነብኝ ነገር ቢኖር የዚህ ጋዜጠኛ ነኝ ባይ አሰራርና የአንዳርጋቸው ጽጌ መመሳሰል ነው ፤ ጋዜጠኛው ከወያኔ ጋር ሲበላና ሲጣጣ "የቡርቃ ዝምታ" ብሎ ሕዝብና ሕዝብን የሚያጨራርስ ፤ ነገር ግን ወያኔን የሚያስደስት መጽሐፍ ጻፍኩ አለ ፤ በተመሳሳይ ሁኔታም አንዳርጋቸው ጽጌ ከወያኔ ጋር በሚጨፍርበት ወቅት ወያኔ አለቆቹን ለማስደሰት " የአማራው ሕዝብ ከየት ወዴት" የሚል አማራውን የሚወነጅል መጽሐፍ መሰል ቅራቅንቦ አውጣ ፤ የነዚህን ሁለት ግለሰቦች አንድነት ብትመለከቱ ሁለቱም ለወያኔ በሚያገለግሉበት ወቅት አማራው ላይ የዘመቱና አማራውን ለማስጨረስ ይጥሩ የነበሩ ግለሰቦች ሲሆኑ ፤ ሁለተኛ የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር ደግሞ ሁለቱም ከወያኔ የጥቅም ክፍያ ተገፍተው ሲወጡ ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ አንዱ " የጋዜጠኛው ማስታወሻ" ብሎ ሲወጣ መሰሉ ደግሞ "ነጻ ያልወጣ ነጻ አውጪ" በሚል ርእስ የቀድሞ አለቆቻቸው ላይ መዝመታቸው ነው ። መመሳሰላቸው በዚህ ብቻ አያበቃም ተስፋዬ ደብረዘይት ተወልዶ ያደገ ሲሆን ፤ አንዳርጋቸው ደግሞ የዘር ሐረጌ ብሎ ከአማራነት በሙብረቅ ፍጥነት ወደ ኦሮሞነት ተለውጦ ፤ እዚያው

ደብረዘይት አካባቢ የሚገኝ አድአ ተብሎ በሚታወቅ ስፍራ ላይ የዘር አጥንቱን እየቆጠረ ሲከምር አስተውለናል ። ታዲያ እነዚህን ሁለት ግለሰቦች የሆራ (የደብረዘይት ሃይቅ) ቆሪጥ በቀትር ላይ ተቆራኝቷቸው ይሆን ወሽካታ እንዲሆኑ ያደረጋቸው? ወይስ በውሸት ጭቃ ተቦክተው በፍርሃት ተለስነው የተሰሩ አስቂኝ አሻንጉሊቶች ስለሆኑ?

የጋዜጠኛው እንጉርጉሮ ፦

ከደትና ቅጥፈት ፤ ሆኖ ፤ ድሬም ማጌ
እኔን የሚመስል ፤ ፈልጌ አስፈልጌ
አውሮፓ ተገኘ ፤ አንዳርጋቸው ጽጌ ።

እንዲህ ነው እንግዲህ የዘመናችን ታጋዮች "ሲሞቅ በማንኪያ ሲበርድ በእጅ" እያሉ ግራ ሲያጋቡን ፤ እኛም እንደ ሚታረድ ከብት እየተነዳን ግርግማቸው እየገባንላቸው ፤ ዘመን ያፈራቸውን አራዳዎችን እያጀብን ፤ የኛ የትግል መሪዎችና ጀብደኞች እያደረግን ፤ መልሰን መላልሰን አምባገነኖችን በላያችን ላይ እየሾምን ዘመን ወደማይሽረው ባርነት በወዶገባነት እራሳችንን አሳልፈን እንሰጣለን ። ጉሮ ወሸባዬ የምንዘፍንላቸው ፤ ያልሆኑትን የምንከባቸው ፤ እኛው ነን ። በየጊዜው አድርባዮች እየተነሱ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨት የሚያደርጉትን እየተመለከትን ፤ አንዴ የአማራው ሕዝብ ከየት ወዴት ሲሉን ፤ አንዴ የቡርቃ ዝምታ እያሉ ሲያፌዙብን ፤ አገራችን ኢትዮጵያን የደም ገንዳ ሆና ለማየት ያልተቆጠበ ጥረት ሲያደርጉ ፤ እኛስ መቼ ነው ለሐገራችንና ለሕዝባችን እንቆረቀራለን የምንል "የኢትዮጵያ ሕዝብ ከየት ወዴት" "የኢትዮጵያ ዝምታ" ብለን በአንድነት አገራችንንና ህዝባችንን ከቀን ጅቦች ለመታደግ እጅ ለእጅ ተያይዘን የምንነሳው?

ድል ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ!!